# የአማራ ህዝብ በትግሬዎች ሴራ ተሸንፏል ወይ ?

**ቤተ አማራ፤ ሰኞ ነሐሴ 9 ቀን 2008 ዓም (Mon August 15, 2016)**

**(https://www.facebook.com/permalink.php?story_fbid=1663966693923682&id=100009311015491)**

**አንድ ፡ - #የአማራ ህዝብ በትግሬዎች ሴራ ተሸንፏል ወይ ?**

"አማራ እንደ ህዝብ በትግሬ ህዉሃት አገዛዝ ተምበርክኮ ፈጽም የተባለዉን ሁሉ እየፈጸመ ያለ ህዝብ ነዉ። ታሰር ሲባል እየታሰረ፡ ተኛ ሲባል እየተኛ፡ ተሰለፍ ሲባል እየተሰለፈ፡ ዋሽ ሲባል እየዋሸ፡ ልግደልህ ሲባል ቀድሞ እየሞተ" ይለኝ ነበር ጥብቅ የልጂነት ጓደኛየ። እኔም ትንሽ ስጋ እንደመርፌ ትወጋ ሁኖብኝ ይሁን? ወይም እንደ ጓደኛየ ግማሽ አማራ ስላልሆንኩኝ ፍትሃዊነት ጎሎኝ ይሁን ሽንፈቱን ላለመቀበል ለረዥም ጊዚያት አንገራግሪያለሁ፡፡ ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ የልጁ ሃሳብ ትክክለኛነት ዘግዬቶም ቢሆን እዉነት ነዉ ብየ የምቀበልበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። የአማራ ህዝብ ለትግሬ አገዛዝ እንደተንበረከከና ዋና ዋና የሚባሉት አማራዊ እሴቶቹ ሙልጭ ብለው እንዲደረመሱ ባለፉት አርባ አመታት በስፋት በጽንፈኛ ትግሬዎች ተሰርቷል። በትግሬ የበላይነት ሙሉ ለሙሉ በተያዘዉ መንግስት አማራ ሁኖ አልተደቆስኩም የሚል ሰዉ ካለ ፤ እርሱ የአእምሮ ጤና የጎደለዉ ካልሆነ በቀር ማሰብ የሚችልና ጥቂትም ብትሆን ቀለም የቆጠረ ሰዉ የሚረዳዉ ነዉ። ዞን ዘጠኝ ከምንኖረው ተነጥለዉ በሆዳቸዉ ገንዳ ውስጥ ተቀስፈዉ የተያዙት ብአዴኖችም ቢሆኑ በጓዳ ከቤተሰቦቻቸዉና ከቅርብ ዘመዳቻቸዉ ጋር የአማራን ሽንፈት የሚያንጎራጉሩት የፖለቲካ ንስሃ ነዉ።

ምን አልባት የአማራዉ ህዝብ ተሸነፈ ወይም አልተሸነፈም ለማለት መመዘኛወቹ ምንድን ናቸዉ? ሊባል ይችል ይሆናል። ይህን ለማስረዳት በመጀመሪያ በሶስት መልኩ ሁለት ህዝቦች ወደ ፍልሚያ ወይም ፍትጊያ ዉስጥ ሊገቡ ይችላሉ ፡ -

**አንደኛ** ፡ - ሁለቱም ህዝቦች በሚያዉቁት ታሪካዊ ወይም ቁሳዊ ምክኒያትና ተቃራኒ ፍላጎት ሊሆን ይችላል።

**ሁለተኛ** ፡ - በአንደኛዉ የህዝብ ወገን በሚመጣ ግልጽ ጠብ አጫሪነትና ጭቆና ሊሆን ይችላል።

**ሦስተኛ**:- አንደኛዉ የህዝብ ወገን በሚስጥር በተጠበቀና አደገኛ ሴራ ሲያሴር። ነገር ግን ተቃራኒ ተብሎ የተፈረጀዉ ህዝብ የተደገሰለትን ነገር በማያዉቅበት መንገድ ሊሆን ይችላል።

ታዲያ አማራዉ በየትኛዉ መንገድ ከትግሬዉ ጋር ፍትጊያ ዉስጥ ገብቶ ነዉ የተሸነፈዉ? የሚለዉ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የአማራዉ ህዝብ ከረዥም ጊዜ ታሪካዊ ዳራ አንስቶ ብዙ ግፍና በደል በትግሬዉ ህዝብ አማካኝነት እየተፈጸመበት ያለዉ በሶስተኛ ደረጃ በተቀመጠዉ አደገኛ ሴራ ነዉ። በአጠቃላይ አማራዉ ፍልሚያ ዉስጥ መኖሩን ሳያዉቅና ሳይረዳ በተቀነባበረ ግለሰብባዊ፡ ቡድናዊና ድርጂታዊ የዘር ጥቃት የትግሬ ህዝብን ይሁንታ ሙሉለሙሉ ባገኘዉ ህወሃት በሚዘገንንና በሚያንገሸግሽ መልኩ ለተከታታይ አርባ ዓመታት የግፍ ግፍ ተፈጽሞበታል። በዚህ ጽሁፍ የረዥም ጊዜዉን ታሪክ ማንሳቱ ለአማራዉ ህዝብ የተጋድሎ ፍልሚያ የሚፈይደዉ ነገር ስለማይኖርና አሁን ያለዉ የአማራ ህዝብ ትዉልድ እየደረሰበት ያለዉ ግፍና መከራ ለነገ የማይተዉ ስለሆነ በቅርቡ የትግሬዉ ህወሃት በአማራ ህዝብ ላይ የፈጸመዉን የለየለት ስልታዊ የዘር ማጽዳት ወንጀልና ሁለንተናዊ ጭቆና ማንሳቱ ተገቢ ይማስለኛል።

አምባቢወቼ በመጀመሪያ ይህን ጽሁፍ ስጽፍ የትግሬ ህዝብና ህወሃት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸዉ ብየ በማመን ነዉ። ስለዚህ ትግሬ ስል ህዉሃት፤ ህወሃት ስል ትግሬ ለማለት ፈልጌ እንደሆነ እንድተረዱልኝ እፈልጋለሁ። ለዚህ ማረጋገጫ ብዙ ሃሳብ መደርደር አያስፈልግም ። በ1997ዓ.ም የተካሄደዉ የኢትዮጵያ ምርጫ ዉጤት ያሳየዉ ሃቅ ቢኖር ትግሬ ህዉሃት፤ ህወሃትደግሞ ትግሬ መሆኑን ነዉ። በዛ ታሪካዊ ምርጫ የአዲስ አበባ ህዝብ ሙሉለሙሉ የመረጠዉ ፓርቲ ቅንጅትን ሲሆን፤ የትግሬዉ ህዝብ ደግሞ ህወሃትን መርጧል። ይህን ለማሳያነት አነሳሁት እንጂ የትግሬ ህዝብ ሙሉለሙሉ የበላይነት በያዘበት የኢሃዴግ ፓርቲ የስልጣን ምንጫ እንደሆነ የአደባባይ ሚስጢር ነዉ።

ለነገሩ በወርሃ የካቲት 1967ዓ.ም በአማርኛ ቋንቋ በተጻፈዉ የህወሃት ፍኖተ ንድፍ ጥራዝ ዉስጥ የመጀመሪያዉ አላማና ስራዉ ይልና እንደወረደ እንደሚከተለዉ አስፍሮታል :

“የትግራይ ህዝብ ብሄራዊ ትግል ጸረ-አማራ ብሄራዊ ጭቆና፡ ጸረ-ኢምፔሪያሊዝም እንዲሁም ጸረ-ንኡስ ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለዉጥ ነዉ። ስለዚህ የአቢዎታዊዉ ትግል አላማ ከባላባታዊ ስርአትና ከኢምፔሪያሊዝም ነጻ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ማቋቋም ይሆናል።”

ይህንንም አላማ ለማሳካት የትግሬዉ ህዝብ ተዋግቶ በለስ ቀንቶታል። ታዲያ በለስ ከቀናቸዉ በኋላ ነጻ መሬታቸዉን ይዘዉ ቢገነጠሉ ለቀሪዉ ኢትዮጵያዊ እጂግ በጣም ጥሩ ነበር። ነገር ግን የትግራይ ሪፓብሊክን ለመመስረት በስዉርና በሴራ እንጂ በጉልበት በወቅቱ ቢሞክሩት ብዙ እርቀት እንደማይጓዙ የተረዱት ይመስላል። ስለሆነም የሚያቦኩትን ፓርቲ አቡክተዉና ጋግረዉ (አህዴድና ደህዴግ ብለዉ) ፤ የነበረዉን ተላጣፊ ኢህዴን ፓርቲ አሳንሰዉ (ብአዴን ብለዉ) ኢትዮጵያን በዋናነትና በምስለኔዎቻቸዉ ለማስተዳደር ሲበቁ፤ የአማራን ህዝብ ደግሞ በስዉርና ግልጽ በሆነ መልኩ ከቀድሞዉ በተባባሰ ሊቀጠቅጡትና ሊያጠቁት አስችሏቸዋል። የትግሬዉ ህዝብ በግልጽ ትብብርና ድጋፍ እንዲሁም ምርጫ ህዉሃትን በይሁንታ መቶበመቶ ያለምንም ደም መፋሰስና ተቃዉሞ እየመረጠ በአማራዉ ህዝብ ላይ ለአርባ አመታት የፈጸመዉ የግፍ መጠን የትየለሌ ቢሆንም በሚቀጥለዉ ጽሁፌ በግርድፉ የምታዉቁትን ሃቅ ለአማራዉ ህዝብ የሸንፈት ምልክት ማሳያወች ይሆናሉ ያልኳቸዉን ሴራዎች፡ በደሎችና ግፎች ለማንሳት እሞክራለሁ። ጎበዝ እኔ አማራዉ በደረሰበት በደል ልክ አጸፋ እስካልወሰደ ድረስ ተሸንፏል ባይ ነኝ እንጂ የጹህፌ መነሻ የተጠቂነት ፖለቲካ አይደለም።

ገጣሚ : - ደበበ ሰይፉ በቋጠረዉ ግጥም ልሰናበታችሁ

በቀበሮ ጉድጓድ - ቀበሮ መስሏቸዉ፤
ዉሾቹ አጓሩ - በዛ ጩኸታቸዉ፤
አይ የዉሾች ነገር - ማን በነገራቸዉ፤
አንበሳ እንደሆነ - የሚጠብቃቸዉ።

**#የአማራተጋድሎ ይፋፋም !**

**ሃምሌ 9/2008 ዓ.ም**